ይሁዳ የመረጠው ‹ጌታ›

ይሁዳ ጌታውን አሳልፎ ሊሠጥ ከመሔዱ ከሰዓት በፊት ጌታችን በቢታንያ በለምጻሙ _ ስምዖን ቤት ተገኝቶ ነበር፡ ዘማዊት የነበረችው ባለ ሽቱዋ ማርያም ግን ይህንን ስትሰማ በለምጻሙ ስሞን ቤት ሳይጠየፍ ከተገፕና ከፈወሰው የእርስዋንም የነፍስዋን ዕድፍ እንደሚያነጻላት, ተስፋ አድርጋ ገሰገሰች፡: በፍጹም ንስሓና የልብ መሰበር ወደ ጌታችን ቀርባ በውድ ዋጋ የገዛችውን የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ሽቱ ያለ አንዳች ስስት በክርስቶስ ላይ አፈሰሰችው:: ቤቱ በናርዶስ ሽቱ መዓዛ ተሞላ፡፡ የሴቲቱንም ንስሓም ጌታችን እንደ ሽቱው በጎ መዓዛ ተቀበለላት፡፡ ይህ የሽቱ መዓዛ ግን ለአስቆሮቱ ይሁዳ አፍንጫ አስደሳች መዓዛ አልሆነም፡፡

<<ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ፣ ለእነዚያም ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን>> የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስ ቃል በማጣቀስ ቅዱስ አውግስጢኖስ እንደተረጎሙት (፪ቆ. ፪+፲፮) ሴቲቱ ካፈሰሰችው ሽቱ የሚወጣው የሕይወት ሽታ ለአስቆሮቱ ይሁዳ የሞት ሽታ ሆነበት, የሽቱው መዓዛ የአንዲትን ነፍስ ወደ እግዚአብሔር መመለስ የሚያውጅ መዓዛ ነበር:: የሰማይ መላእክት በአንዲቱ የባከነች ኃጥእት ነፍስ መመለስ ደስ ሲሰኙ ይሁዳ ግን ደስ አልተሰኘም ያሳሰበውም የሽቱው መባከን ነበር፡፡ ከዚህች ሴት ይልቅ የይሁዳ ጭንቅላት ሲያሰላ የነበረው ሽቱው አሁን ባለው ገበያ ስንት ያወጣ ይሆን እሚል ነበር (ሉቃ. ፱+፶፩) ፡የአንዲት ነፍስ ዋጋዋ ከዓለም ሁሉ ይበልጣል ይሁዳ ግን ከዓለም

ከሚበልጠው የሰው ነፍስ መመለስ ይልቅ የአንድ ብልቃጥ ሽቱ ጉዳይ አንገበገበው::<< ይህ ምንድን ነው? ሽቱው ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው አለ? >>

በጌታዋ ፊት በተሰበረ ልብ መጥታ ራስዋን ያዋረደችውን ሴት የሚያሸማቅቅ ,የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማት የሚያደርግና ጌታችን እንዳለው <<**የሚያደክም**>>ንግግር ተናገረ::

ስለ ድሆች ማሰብ መልካም ነው:: ጌታችንም ከሚቀበል ይልቅ የሚሠጥ ብፁዕ ነው ብሎ አስተምሯል ፣ለድሆች ምጽዋት እንዲሠጥ ማዘዙም ሐዋርያቱ ሲያዩት የኖሩት ልማድ ነበር:: (ሐዋ ፳+፬: ዮሐ.፲፫+፳፯) ሰዎችን መርዳት ግን ነፍሳቸውን ከማዳን ሥራ አይበልጥም፡በቤተ ክርስቲያን የሚደረግ ማንኛውም የርዳታ ሥራ ሁሉ ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር አስተምሮ ከመመለስ አገልግሎት እንዲሰጠው ማድረግ የይሁዳን አስተሳሰብ ማራመድ ይሆናል:: እንደ የበለጠ እውነታው ከሆነ ማ ይሁዳን ያስጨነቀው የድሆች ጉዳይ አልነበረም ቅዱስ ዮሐንስም እንዳለው ***ይህንም የተናገረው ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆ ተገድዶላቸውአይደለም :ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወሰድ ስለ ነበረ ነው, በማለት እውነታውን ጽፎልናል::*** (ዮሐ. ፲፪+፮).